


# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

## ሰላምታ አሰጣጣችን “ንጹሕና እውነተኛነት” ይኑረው

**በቃል የሚጠና፡- 2ኛ ቆሮ. 12፥9**

*“ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና፥ ሰላም ለእናንተ ይሁን” ፊልጵ. 1፥2)።*

### 1 ክርስቲያናዊ የሆነ “ሰላምታ” እንድንሰጣጥ ቃሉ ያዛል

*“ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን”* ሲል፥ ጳውሎስ *የግሪኮችና የአይሁዶችን* ዓይነት ሰላምታ እየደባለቀ መስጠትልማዱ እንደነበረ ቀደም ሲል በጻፋቸው ደብዳቤዎች ላይ በግልጽ እናያለን። *“ጸጋ”* ወይንም *“ካሪስ”* የሚለው ቃል *የግሪኮች* ሲሆን፥ *“ሻሎም”* ወይንም *“ሰላም”* የሚለው ቃል ደግሞ አይሁዶች ሰላምታ የሚለዋወጡበት ቃል ነው። ጳውሎስ በወቅቱ ለነበሩት መጋቢዎች በጻፋቸው ደብዳቤዎች ላይ ግን *“ምህረትን”* በመጨመር *“ጸጋና ምህረት፥ ሰላምም ይሁን”* በማለት ሰላምታውን ሲገልጽ እናያለን (1ኛ፥ ጢሞ. 1፥2)። ለክርስቲያኖች *“የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ለእናንተ ይሁን”* ብሎ ከመመኘት የተሻለ ሌላ ምን ዓይነት ሰላምታ ይገኝ ይሆን? ጳውሎስ ምንጊዜም የማያምንበት፥ ከልቡ ያልወጣ ሰላምታ መስጠት የሚፈልግ፥ በቃላት ብቻ የሚጫወት ሰው እንዳልነበረ እናውቃለን። ጳውሎስ ራሱ ምሳሌ ሆኖ ክርስቲያኖች ከልብ የሆነ ሰላምታ እርስ በርሳቸው እንዲሰጣጡ ይመክራል። ለተሰሎንቄ አማኞች *“ከወንድሞች ሁሉ ጋር በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ”* ይላቸዋል (1 ተሰሎ. 5፥26)። እንዲሁም ለቆሮንቶስ አማኞችም *“በተቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ”* ይላቸዋል (2 ቆሮ. 13፥12)። ጳውሎስ ብቻ ሳይሆን ሐዋርያው ጴጥሮስም በክርስቲያናዊ ሰላምታ አሰጣጥ ያምናል። *“በፍቅር አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ”* ይላል (1ኛ ጴጥ. 5፥14)። ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ሰላምታ እንዲሰጣጡ ጳውሎስም ሆነ ጴጥሮስ የሚያዙት፥ የፍቅራቸው መግለጫ እንዲሆን እንጂ የሃይማኖት ሥርዓት አድርገው እንዲወስዱት አይደለም። በዘመኑ ያለነውም ክርስቲያኖች ስንገናኝ በመተቃቀፍ፥ በመሳሳም ሰላምታ የምንሰጣጣው ከሥርዓት ውጪ መሆናችን አይደለም። ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ነገር ቢኖር፥ ሰላምታችን ከልብ የወጣ፥ ወይንም ሥርዓት ለመፈጸም ብቻ መሆሆን አለመሆኑን ነው።

### 2 የእግዚአብሔር ቃል የማይደግፈው “ሰላምታ” አሰጣጥ አለ?

የክብር ሰላምታ እንዲሰጣቸው የሚፈልጉ አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች በክርስቶስ ዘመን እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። አግባብ ያልሆነ ሰላምታ የሚሰጡትንም ሆነ የሚቀበሉትን ክርስቶስ ይነቅፋቸው እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን። *“በምኩራብም የከበሬታ ወንበር፥ በገበያም ሰላምታና መምህር ሆይ! መምህር ሆይ! ተብለው እንዲጠሩ ይወዳሉ። እናንተ ግን መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፤ መምህራችሁ አንድ ስለ ሆነ እናንተም ሁላችሁ ወንድማማቾች ናችሁ”* ይላል (የማቴ. 23፥7)። የክብር ሰላምታ የጠማቸው፥ ሰው ሁሉ እጅ እንዲነሷቸው የሚፈልጉ፥ የሚፈልጉትን ካላገኙ የሚያኮርፉ፥ የከበሬታን ቦታን በአደባባይም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማግኘት የሚፈልጉ አማኞች የነበሩት ጥንት ብቻ ሳይሆን፥ በዘመናችንም ሞልተዋል። ከበሬታን በመፈለግ ራሳቸውን ከሆኑት በላይ ትልቅ አድርገው የሚያቀርቡ፥ በመሳላል ካልሆነ በስተቀር የማይደረስባቸው፥ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በዘመናችን በየቦታው ብዙዎች እንዳሉ እናውቃለን። ጳውሎስ *“እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ”* ሲል፥ “ለክርስቶስ የሚገባውን ክብር ለሰው ስጡ” ማለት እንዳልሆነ ማወቅ ይገባናል።

በዘመናችን ከልብ ያልወጣ ሰላምታ ሲለዋወጡ የሚታዩት ዓለማውያን ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያኖችም ናቸው። በአገራችን አንዳንድ ሰዎች እንግዳ ሲመጣባቸው፥ እንግዳውን የሚቀበሉት *“በምትኩት! ግባ/ግቢ!”* ፣ *“አፈር ስሆን ጎራ በሉ!”*፣ *“እንኳን ደህና መጣህ/መጣሽ! ግባ/ግቢ”* በማለት ነው። አንዳንዶች ይህን ይበሉ እንጂ፥ ከልባቸው የወጣ፥ እውነትነት ያለው ሰላምታ እንዳልሆነ እናውቃለን። እቤታቸው ሲመጣ ይህን ዓይነቱን ሰላምታ የማሰጡት በጣም የሚወዱትን ሰው ብቻ ሳይሆን፥ ሊያዩት የማይፈልጉትን፥

በጣም የሚጠሉትን ሰው ጭምር ነው። በዚህ ዓይነት ሰላምታ የተሰጠውም ሰው ቢሆን፥ ሰላምታ አሰጣጣቸው እውነትነት እንደሌለው ያውቃል። ቋንቋውና አባባሉ ከላይ የሰማነውን ዓይነት አይሁን እንጂ፥ ከልባቸው ያልወጣ፥ ወይንም እውነት ያልሆነ ሰላምታ ሲሰጡ፥ እንዲሁም ሲተቃቀፉ የሚታዩት ዓለማውያን ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያኖችም ጭምር ናቸው።

አንዳንድ የዘመኑ ክርስቲያኖች ተባልተን፥ ተነካክሰን፥ ጥርስ ተሰባብረን ከተለያየን በኋላ በሌላ ጊዜ ስንገናኝ እውነትነት የሌለው ፈገግታ እያሳየን ተቃቅፈን ሰላምታ መሰጣጣት፥ *“ወንድማችን፥ እህታችን”* መባባሉ፥ መሳሳሙ ልማዳችን ሆኗል። ይህንን ዓይነት ሰላምታ የምንሰጣጣው “ተበደልን” የምንለውን ትተን፥ ይቅር ተባብለን ሳይሆን፥ በልባችን ቂምና ቅሬታ እንደታቀፍን ነው። በአንዳንድ የዘመኑ ክርስቲያኖች ዘንድ የክርስትና እምነት “ይቅርታ መስጠትና” መቀበል የሌለበት ሆኖ መታየቱ በጣም ያሳዝናል። በልባችን ቅሬታና ቂም ይዘን ተቃቅፎ መሳሳሙ፥ “ጌታ ይባርክህ” መባባሉ፥ ግብዝነት እንደሆነ መገንዘብ አያቅተንም። ጌታ ኢየሱስ ድካማችንን ይረዳል፤ ግብዝነታችንን ግን በጣም ይጠላል።

## 3 “ጸጋ” ማለት ምን ማለት ነው?

ጳውሎስ በሰላምታው ውስጥ *“ጸጋ፥”* ሲል ምን ማለቱ ይሆን? *“ጸጋ”* የሚለው ቃል ሁለት ዋና ዋና ሀሳቦችን ይዟል። “ጸጋ“ የሚለው ቃል *“ካሪስ”* ከሚለው የግሪክ ቃል የወጣ ሲሆን፥ ትርጉሙም የሚያስደስት (ቻርም) ማለት ነው። ስለዚህ ጳውሎስ “ጸጋ” ሲል፥

*1ኛ) የክርስትና ሕይወት ደስታ ያለበት መሆኑን መግለጹ ነው።* የክርስትና እምነት ማንንም የማይስብ ወይንም የማይማርክ፥ ጭፍግግ ያለው አይደለም። ጳውሎስ የፊልጵስዩስን አማኞች *“ጸጋ ለእናንተ ይሁን...”* ሲላቸው፥ ደስታ የሞላበት የክርስትና ሕይወት እንዲኖራቸው ምኞቱን ሲገልጽላቸው ነው።

*2ኛ) “ጸጋ” የሚለው ቃል ከስጦታ ጋር የተያያዘ ነው። “ጸጋ”* ሁሉን ማድረግ ከሚችለው ከእግዚአብሔር ከራሱ ብቻ ሊመነጭ የሚችል ነው። ለጋስ ከመሆኑ የተነሳ ዋጋ ሳያስከፍል፥ ወይንም በነጻ ለማይገባው ሰው በሰፊው ስጦታን መስጠት ማለት ነው። የደህንነታችን ምንጭ ወይንም መነሻው ጸጋ ነው። *“...በጸጋ ድናችኋል”* ይላል (ኤፌሶን 2፥5)።

## 4 ከዚህ ክፍል የምናገኘው ትምህርት

### *(ሀ) ሰላምታችን እውነተኛነት ያለው መሆን ይገባዋል።*

በልባችን ቅሬታ ይዘን መተቃቀፋና መሳሳሙ፥ ክርስቶስን እንድንመስል አያደርገንም። በልቡ ተንኮል ይዞ በመሳም ለክርስቶስ ሰላምታ ለመስጠት የሞከረው ይሁዳ አስቆሮቱን አንረሳውም። የልቡ ተንኮል ስለገባው ኢየሱስ ይቁዳ አስቆሮቱ “የምስመው እርሱ ነው፤ ያዙት ብሎ ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር። ወዲያውም ወደ ኢየሱስ ቀረበና መምህር ሆይ! ሰላም ለአንተ ይሁን ብሎ ሳመው” (የማቴ. 26፥48-50)። የእኛስ ሰላምታ አሰጣጣችን ይህንን ይመስል ይሆን?

### *(ለ) ጸጋ “የደህንነታችን ምንጭ ነው።*

“ደህንነት” ስጦታ፥ ወይንም በነጻ የሚሰጥ ባይሆን ኖሮ፥ ሰው ፈጽሞ ሊያገኘው የማይችለው ይሆን ነበር። *“ጸጋ“* የሚለውን ቃል ስንሰማ መረዳት ያለብን አንድ ነገር ቢኖር፥ ተወዳጅ የሆነውን የክርስትና ሕይወት፥ ለማይገባን ለእኔና ለእናንተ የሰጠው እግዚአብሔር እንደሆነ ነው።

### *(ሐ) ጳውሎስ “ጸጋ ለእናንተ ይሁን...”*

በማለት ለፊልጵስዩስ አማኞች ሰላምታ ሲያቀርብ፥ “ደስታ ያለበትን የክርስትና ሕይወት እንዲሁ በነጻ ሊሰጣቸው ከሚችለው ጌታ እንዲያገኙ መመኘቱን ሲገልጹ ነው።

### *(መ) ለአገልግሎት የሚያስታጥቀን፥ እንዲሁም መሆን የምንችለውን እንድንሆን የሚያስችለን የእግዚአብሔር ጸጋ ነው።*

ይህንን የተረዳው ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል *“ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም፤ ከሁላቸው ይልቅ ግን ደከምሁ፤ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም”* (1ኛ ቆሮ. 15፥11)። ጸጋ የደህንነታችን ብቻ ሳይሆን፥ የመንፈሳዊ ኃይላችን ወይንም ብርታታችንም ምንጭ ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን *“እንግዲህ ልጄ ሆይ! አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ”* ያለው ለዚህ ነው (2 ጢሞ. 2፥1)።

---




**የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብምን ስሜትና አሳብ ይመረምራል።**

(ዕብራውያን 4፥12)




## ሀ የመልእክቱን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት

① ጳውሎስ “ጸጋና ሰላም” የሚለውን ሰላምታ አሰጣጥ ከየትኛው ባህል ያገኘው ነው?

② ጳውሎስ ለመጋቢዎች በጻፋቸው መልዕክቶቹ ላይ የምናየው የሠላምታ አሰጣጡ ከዚህኛው በምን ይለያል? (1 ጢሞ. 1፥2)።

③ ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ስለ ሰላምታ አሰጣጥ የሚመክረው ምንድነው? (1 ተሰሎ. 5፥26፥ 2 ቆሮ. 13፥12)

④ ጴጥሮስስ ስለ ክርስቲያናዊ ሰላምታ አሰጣጥ ምን ይላል? (1 ጴጥሮስ 5፥14)

⑤ የክብር ሰላምታ ስለሚጠሙ ሰዎች ኢየሱስ ምን ይላል? (የማቴ 23፥7)

⑥ ጸጋ ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. __________

ለ. __________

⑦ ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ምዕመናንን *“ጸጋ ለእናንተ ይሁን”* ሲላቸው ምን ማለቱ ይሆን?

⑧ ለአገልግሎት የሚያስታጥቀን፥ እንዲሁም መሆን የምን ችለውን ሆነን እንድንገኝ የሚያስችለን እንደ ጳውሎስ አነጋገር ምንድነው? (1 ቆሮ. 15፥11)

⑨ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን *“እንግዲህ ልጄ ሆይ! አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ”* (2 ጢሞ. 2፥1) ሲለው፥ “ጸጋ” የሚለውን ቃል ዝም ብሎ መጠቀሙ ነው? ወይንስ ምክንያት አለው?

⑩ ይሁዳ አስቆሮቱ ክርስቶስን የሳመበት ምክንያት ምን ነበር? (የማቴ 26-48-49)

## ለ በዚህ ክፍል ውስጥ ያገኘነውን ትምሕርት በግል ሕይወታችን ለመለማመድ...

① በክርስቲያኖች ሰላምታ አሰጣጥ ውስጥ ቅር የሚለኝ ነገር ......


② በራሴ ሰላምታ አሰጣጥ ቅር የሚለኝ ነገር.....

③ በውስጤ ቅሬታ ይዤ ዝም ብዬ ሰላምታ የምሰጣቸው ሰዎች አሉ። እነርሱም .....

④ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይህንን ለማስተካከል እርምጃ ለመውሰድ ያሰብኩት.....

⑤ የእግዚአብሔር ቃል ደስ እንዲለን ቢያዝም፥ አንዳንዶቻችን ብዙ ጊዜ ደስታ የሸሸን ነን። ደስታን እንድታጣ (እንድታጪ) ምክንያት የሆኑብህ/የሆኑብሽ ነገሮች ምንድናቸው?

⑥ በሕይወትህ/በሕይወትሽ የተፈጸሙ፥ "በእግዚአብሔር ጸጋ ነው" የምትላቸው/የምትያቸው ነገሮች አሉ?



የትምሕርቱ አዘጋጅ
መለሰ ወጉ

# ስንቅና ትጥቅ

## በኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ተዘጋጅቶ፥ በየሁለት ሳምንቱ እየታተመ የሚወጣ ግላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው።

**Ethiopian Outreach Ministry**
**P.O.Box 2241**
**York, PA 17405**
**U.S.A.**
**Phone/Fax: (717)846-2041**
**E-Mail: eomusa@aol.com**
**Internet Address:**
**www.ethiopianoutreach.com**

## የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አድራሻ